"R.H.2003 የኢትዮጵያውያን ጥያቄ ሳይሆን የኢትዮጵያ ጠላቶች ጥያቄ ነው።"

እኔም የምጋራው ነኝ። አገራችን የነፃነት ፋናዋ ተረስቶ በአሜሪካ የዴሞክራቶች ኰንግሬስ ሃሳብ መብቷ እንዲነካ በማለት የሆልጋኖች ጩኸት ዓለምን አናግቷል። በፈለገው መንገድ ቢታሰብም  የኢትዮጵያ አገልግሎት ለአሜሪካና ለፍላጐቷ ከፍተኛ አስተዋፆ አድርጓል። አሜሪካኖች ለምሥራቅ አገር የአረብ ኤሚራቶችና ለግብጽ ለእስራኤሎች ያደረገችው ዓይነት ወታደራዊና አገራዊም እርዳታ ለኢትዮጵያ አላደረገችም ለምን?

አሁን አሜሪካ ስለ አሜሪካ ችግሩዋ ተረድቷትና የራሷንም ችግር ለማስወገድ በሞቃዲሾ ኢትዮጵያ የወሰደችውን የመሰለ ሁኔታን እነዚህ በ60 ቢሊዮን ዶላር የተገመተ በጐ አድራጎት የተደረገላቸው የኢትዮጵያን የሳምት ችግሮችን ችሎ ስለ ዓለምም ሰላም ካቅሟ በላይ በማሰብ እየተዛተባት ያደረገችው ከፍተኛ ውለታ የአሜሪካንንም ኮንግረስ ሆነ የአሜሪካን መንግስት ችህምር ሊያመሰግኗትና ብሎም ከዚህ ከያዛት አዙሪት የድህነት ስቃይ ሊያወጧት በተገባቸው ነበር።

ነገር ግን የኰንግሬሷ አፈ ጉባኤ ይህን ጉዳይ በህዝቡ በሆልጋኖቹ እየተፈረመ ፔቴሽኖችና የፋክስ መልክቶች የስልክ ጥሪዎች እንዲደርሳት የምትፈልግ ወይዘሮ ትመስላለች። ይህን የተያዘውን ሲሰተም ኢትዮጵያዊያን ሳይሆኑ ስለ ኢትዮጵያ የሚያውቁ ሻዕቢያዊያኖች እንደሆኑ አሌ የማይባልለት እውነታ ችህምር መሆኑን የአገር ዜጐቿ ሁሉ ሊገነዘቡት ይገባል።

እንግዲህ ትዝብቱ እምን ላይ ነው ተብሎ ቢሰላ እውነት አሜሪካኖች ከአጠገባቸው አብሯቸው የተሰለፈው እነማንና ማናቸውስ ብለው የሚያስቡ ይሆኑ ይሆን ወይስ እንደዘመኑ ሆልጋኖች እንደ ዋሽንግተን ፖስትና እንደ ኒውዮርክ ታይም ሰዎች ኢትዮጵያን እያራከሱ መትሳፍ ይቀጥሉበት ይሆን? እነዚህ ጥያቀዎች የሚመለከተው የምስተር ደብሊው ቡሽን አስተዳደር በተለይ ይመለከታል።

የቀራቸው ጽልጣናቸው ሊያልቅ ምናልባት 14 ወሮች ቢቀሯቸው ነው።።እነኝህ ጊዜዎች ደግሞ ውለታ የዋሉላቸውን አገሮች አስታውሰው በመጸረቱ ኢትዮጵያ እስካሁን 40 ዓመት ሙሉ በጦርነት ላይ ሆና ትገኛለች። እነኛም ጦርነቶች ራሳቸው ምስተር ቡሽ የተሰለፉለት ዓለም ዓቀፍ ቴሬሪዝምና ብሎም አሸባሪነት ነው። ያን አሸባሪነት ኢትዮጵያ እስካሁን እየተፋለመች ትገኛለች።

ታዲያ ምስተር ቡሽና አገራቸው ካቢነአቸው ማሰብ ያለባቸው ለኢትዮጵያ የማርሻል ፕላን የመሰለ ድጋፍ ያለው ችሀርሶም ያችን አገር ከድህነቷ ሊያላቅቅና ብሎም ወደስልጣነ ውስጥ የሚያስገባት ሊያስገባትም የሚችል ከፍተኛ እስከዛሬም የጀርመኒና ከጃፓን በስተቀር ያልተሰጠ እርዳታና በ100 ዓመት ለሚያህል ጊዘም ተከፍሎ የሚችህረስ እርዳታና ብድር ሰተው ኢትዮጵያን ከያዛት ችግር መገላገል ይገባቸዋል በሚል ነው?

እንግዲህ ያሲስተካከል አሁን እየጮኩ የሚስተዋሉት አራጋቢ ሆልጋናዊያን ሁሉ ጥለዋት ከሸሹብት አገር ወደ አገራቸው ገብተው እንደቀረው ዓለም ሰርተው ራሳቸውንም ችለው በገዛ አገራቸውም ላይ ተዝናንተው የሚኖሩበት እቅድን ይፈጥራላቸውል ማለት ነው። አንድ አገር ካላት ሁሉም ይወዳታል። ብሄራዊ የተፈጥሮ ሃብቷንም በመፈለግ በማውጣት ለዓለም የንግድ የንግድ ድርጅት ውስጥ ያለምንም ጣጣና አስቸጋሪ አስተያየቶችንም ጥሳ ተካፋይ ልትሆን ትችላለች። እንግዲህ ያሁሉ ሊሆን የሚችለው የታላቋ አሜሪካ ወይም የምስተር ቡሽ አስተዳደር ስለኢትዮጵያ አስፈላጊዋ ምንድን ናቸው ብለው ሲያስቡ ብቻ ነው?።

አሁን ይሄን R.H. 2003 ካልታየልን ብለው የሚጨቀጭቁት ሰዎች ኢትዮጵያን የማይወኩሉና ብሎም የሌላ ተላኪ መሆናቸውንም ማወቅ ይገባል። ኢትዮጵያዊ የሆነ ሰው ለአገሬ የሚሰጣት ድጋፍ በበለጠ ይቀጥል ብሎ የሚመኝበትና ብሎም መሆን እንዳለበት አስቦ ራሱን የሚያቀርብ እንጅ የኢትዮጵያ ሞትና ረሃብ በሽታዎችን የሚመኝ አይደለም። ይህ ጉዳይ እንደዚህ ችላ ተብሎ መታለፍ የለበትም። የአገር ጉዳይ ከፍተኛው የሚንጸባረቀው የመጀመሪያው የኤኮኖሚ ድቀት እንዳይደር ያንን መከላከል ነው።

እነኝህ የወቅቱ ጥርቅሞች ግን ያንን ማሰብ አያስችላቸውም ፍላጐታቸው ከሰማይ እንደ ታቦተ ጽዮን የተወረወሩና ኢትዮጵያንም እነሱ ብቻ መግዛት እንዳለባቸው የተመረቁ ይመስል የሚያወሩት ወረአቸው ሁሉ ከሥልጣኗ ላይ ለመድረስ ብቻ እንጂ ከዚያ በኃላ በአገራችን ላይ ምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚፈጠርም ሆነ እንደሚመጣባት አያውቁትም። ነገር ግን እነሱ ያሰቡት ሁሉ ጽድቅ እንደሆነ ሌሎቹ የኢትዮጵያ ልጆች የሚያስቡት ከሆነ ኩነኔ የሚሆን አድረገው ይመለከቱታል። እንደዚህ ያለ ከሚያስብ ሰውና ጐረቤት ይሰውራችሁም ያሰኛል። ሁሉንም በየፈርጁ ማስተዋል ሲገባቸው እነኝህ ግን የገዛ እናታችን ናት የሚሏትን አገራቸውን ጡቷን ሲነክሱ በየሰከንዱ ጊዘም ሳይገድባቸው ይስተዋላሉ።

ታዲያ ሆልጋን ጮከ ተብሎ የአገር ልማቷ ሊቋረጥ አይቻለውም እንዲያውም በሚያስቀናና በሚያስመሰግን ለመጪው ትውልድ የሚትረፈረፍ ግንባታና ከድህንነት ጭለማም ውስጥ ያንን አስቀያሚ የድህነትን ማነቆ አውልቆ በመጣል ወደ ጸዳና አስመስጋኝነት ወደአለው የኤኮኖሚ መጸረት መሸጋገር የግድ የሚጠይቅበት ወቅቱ አሁን እንጂ እናም ከዛሬ ሁሉም መጀምር አለበት ነገ ተብሎም ማደር አይኖርበትም። ለህዝባችን እንዲነገር የሚያስፈልግም ጉዳይ ነውና።

ችግሮችን አስወግዶ ለተመጣጠነ እድገት ለማምጣት የሁሉንም ይሁኝታዎች የግድ አስፈላጊ ነው። ያንንም ለማድረግ በአገር ውስጥ የሚገኙ የሁለቱም ክፍል አሳቢዎች ያለው መንግሥትና ተቃዋሚ ፓርቲዎቹ በአገር እድገት እና ዓለም አቀፍ የአገር ደህነቶች ጭምር አብረው ለመስራት መመከር አለባቸው። ካሁን ጊዜ ጀምሮም አንድም ለአገሩ ባዕዳ እንዳልሆነና እንደማይሆንም ጠንቅቀው ሊያውቁት ይገባል። ኢትዮጵያ እስከሌለች ድረስ ፖለቲካም የሚባል የለም። ኢትዮጵያችን ካለችና ተደስታ የምትኖር ከሆነ ግን ፖለቲካውም ተትረፍርፎ በሳይንስ በሶሻል ሲስተም ሕዝባችን እረክቶ ለመታየት መብቃት ይገባዋል። ቀጥሎም ከሁሉም በፊት የህግና ፍትህ ተቋሞች ከማንኛቸውም በፊት ስፍራ ሊሰጣቸውና ሊታሰብበትም ይገባል።

እንግዲህ ይህ ከሆነ በኃላ መታሰብ ያለበት ሁሉም እንደየችሎታው ለራሱና ለቤተሰቡ የሚዳረስ ደሞዝ ይኖረዋል። አምራችም ከሆነ የሚበቃውን ያመርታል። ከፖሊስ ጀምሮ የመንግሥት ባለሥልጣና ግን ጉቦ የሚበላ ከተገኘ እጅከፍንጅም ከተያዘ በሚገባ ያውም ለመቀጣጫ የሚሆን ቅጣት ሊቀጣ ይገባዋል። በዘመድና በስልክ መስራት ሁሉ? ብሎም እየደጋገመ ይህን ጥፋት የሚሰራ ሃላፊም ሆነ ተራ ሰራተኛ ከአለበት ሥራ ይባረራል።የሰረቀውንም ሆነ በጉቦ መልክ የወሰደውን ያጠራቀማቸውን ችህምር ተወርሶ ሃብት ለሌላቸው ወይም ያገሪቱን ሕዝብ የሰሻል ጥያቄዎቻቸውን እንዲያሟሉበት ይደረጋል።

በዚህ ሁኔታ አገራችን ከድህነቷ የምትወጣ ከሆነ አሳዳጊ ያጡ ሕጻናቶችን በመላ ሃገሪቱ በተለይም በአንድ ጠቅላይ ግዛት ውስጥ በመሰብሰብ ከስፖርት እስከ ትምህርታቸውን የሚቀስሙበት ዩኒቨርስቲ ድረስ እዚያውም እየኖሩ ካደጉም በኋላ የሚመራመሩበት ቦታ ይሆናል ማለት ነው። ልክ እንደጃፓንና ራሺያዎች የተመሩ የሚመራመሩበት የተለየ ሰላምና ጸጥታ የበዛበት ክፍል አድገው በዚያውም ወደከፍተኛ ቦታ የሚሸጋገሩበት ቦታ ይሆናል ማለት ነው።

እንግዲህ አገራችን ለመልጸግ እንድትችል ይህን ጐራዳ አስተሳሰብ ማስወገድ ይኖርብናል ማለት ነው። ማንም ይግዛ ጉዳዩ ስልጣን መያዙ ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ ሰው ዜጋ ለአገሬ ዛሬ ምን ሰራሁላት በሚል ሊያስብ ይገባዋል ነው። በዚያ መሃከል መንግሥትም ልክ እንደህቡ ለአገሬ ምን ቀረኝ የማደርግላት ብሎ እንዲያስብ ያደርገዋል ማለት ነው።ከዚያ ይህ መተረማመስ ይቀርና ሁሉም እንደ ወንድም እህትማማች አብሮ እንዲያስብ ያደርገዋል። ችግሮችም ይወገዳሉ። ነገር ግን አሁን በተያዘው አካሄድ እኔ እንጃ ብዙ ጊዜ እንዳይወስድ ያስፈራኛል። መተባበር አቅቶናል። ወሬኞችም ሆነናል። ለምን ይሄስ ይሆናል ተብሎ ሲጠየቁ የሚናገሯቸው ሌ አስተሳሰብ ሆነው ይገኛሉ።ለመሆኑ እነኛ ሰዎች ይህን እንዲናገሩ የኢትዮጵያ ሕዝብስ ፍላጎቱ ነበር ወይ ተብለው ሲጠየቁ መልስ ከመስጠት ይቆጠባሉ። ከኋላ ሆነው ግን ተንኮላቸውንና ሃሚታቸውንም ይያያዙታል? እንግዲህ ይህን ተፈጥሮ ተወደደም ተጠላም መለወጥ ይኖርበታል።

R.H.2003 የኢትዮጵያውያን ጥያቄ ሳይሆን የኢትዮጵያ ጠላቶች ጥያቄ ነው።

Abera Tuffa
ከአበራ ቱፋ
አዲስ አበባ (ጉለሌ አባኮራን ሠፈር)